

በድረ ገጽ ላይ በጥላቻ ንግግር ላይ ርምጃ የምንወስደው ለምን ድን ነው

bildungsstätte
anne frank

ይዘት

ሁሉም ነገር ሰለጠ ዩዎቹ እና አሠራ ጮቹ ነው ?

7ፅ 5

ማንሳት ወይም መከላከል ?

7ፅ 7

የጥላቻው እሳት ሲነሳ ምን መደረግ አለበት ?

7ፅ 9

የኛ ፕሮጀክት

7ፅ 15

ሁሉም ነገር ስለጠዓዎቹ እና አሠራጮቹ ነው ?



ማኅበራዊ ትስስሮች የዕለት ተዕለት ሕይወታችን አካል ናቸው። በትዊተር፣ ፌስቡክ፣ ቲክቶክ ወይም ኢንስተግራም። በመላው ዓለም ከሚገኙ ተጠቃሚዎች ጋር መረጃ እንለዋወጣለን፣ የትርፍ ጊዜ ፎቷችንን እናሳያለን እና ስራችንን እናቀርባለን። ለብዙ ሠዎች ሕይወት ያለማኅበራዊ ትስስር መገናኛ ብዙሀን የሚታሠብ አይደለም።

እንዳለመታደል ሆኖ ይህ የቀን ተቀን ሕይወትም ጥቃትን ያካትታል። የጥላቻ ንግግር የሚባለው በማኅበራዊ ትስስር መገናኛ ብዙሀን ላይ ያሉ ሠዎች ሲዘለፉ ወይም ሲጠቁ ነው - በተለይም የሚመለከታቸው ሠዎች የአናሳ ኅብረተሠብ አባል ሲሆኑ።

ሴቶች ወሲባዊ ዘለፋ ሲደርስባቸው፣ ጥቁሮች የዘረኝነት ስድብ ሲሰደቡ ወይም አይሁዶች ፀረ-ሴማዊ ጥላቻ ሲገጥማቸው፣ የጥላቻ ንግግር እየደረሰባቸው ነው። አሠራጮች በመጀመሪያ ትንኮሳ ለመፈጸም የጥላቻ ንግግር ይፈጥራሉ፣ ጠዓዎች አብዛኛውን ጊዜ በተለያየ ምክንያት ክብራቸውን ሊነኩ በሚፈልጓቸው ሠዎች ላይ ያተኩራሉ።

ይሁን እንጂ መነሻ ምክንያታቸው ምንም ለውጥ አያመጣም: ዋናው ነገር ይህ ንግግር በሠዎች ላይ የሚያሳድረው ውጤት እና በአብሮነታችን ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ነው።

ወተው ወይም መከላከል ?



የጥላቻ ንግግር አንዱ የጥቃት አይነት ሲሆን ውጤቱም አስከፊ ነው። ተጠቃሚዎችን ሊጎዳ፣ ሊያሠቃይ እና ኦንላይን አገልግሎት መጠቀማቸውን እንዲያቋርጡ ሊያደርጋቸው ይችላል።

በግለሠብ ደረጃ፣ የጥላቻ ንግግር ሠዎች ላይ መጥፎ ስሜት ያሳድራል፡ የረጅም ጊዜ ጭንቀት እና ለምሳሌ በተደጋጋሚ የሚከሰት የጥቃት ስጋት፣ ጭንቀት ወይም የእንቅልፍ መዛባት ሊያ ስከትል ይችላል።

በሳብረተሠብ ደረጃ የጥላቻ ንግግር አስቀድሞውኑ ደካማ እና ጭቁናን የሆኑ ቡድኖችንቡ ድኖችን ከሠው ዓይን እንዲሸሹ ሊያደርጋቸው ይችላል።

በመሆኑም የጥላቻ ንግግርን መዋጋት በጣም አስፈላጊ ነው!

እኛ የምንፈልገው ተጠቃሚዎች በድረ ገጽ የሚተላለፍ የጥላቻ ንግግርን እንዲዋጉ ማገዝ ብቻ ሳይሆን፣ አንድ ላይ ሆነን ድረ ገጽ ላይ የሚታይን ጥላቻ የማዳከም ሀሳባዊ ግብንም ታሳቢ ልናደርግ እንፈልጋለን!

የጥላቻው እሳት ሲነሳ ምን መጀረግ አለበት ?



በጥላቻ ንግግር ላይ ተፈጻሚ የሆኑ ስልቶችን ካወቁ፤ ራስዎን እና ሌሎችን መከላ ከል ይችላሉ።

1 በአየር ከሚደረግ ጉዞ እናውቀዋለን: በመጀመሪያ ራስዎን ይከላከሉ፣ ከዚያ ሌሎችን መርዳት ይችላሉ። የግል መረጃዎ ለምሳሌ የት መኖር እና የት መቆየት እን ዳለብዎት የሚገልጽ መረጃ በፍፁም በሁሉም ሠው መታወቅ የለበትም። በዚህ ጉዳይ ላይ ምክር ከዚህ ማግኘት ይቻላል www.kompass- social.media.

2 ትጋት አስፈላጊ ነው፣ ነገር ግን በጣም አድካሚ እና አስ ጨናቂ ሊሆን ይችላል። የሚያነቡት መልዕክት ብቻ ቢሆንም - ለራስዎ ደህንነት ትኩረት ይስጡ። በረዘ መጡጣት ወይም ማቋረጥ። ሁልጊዜም የእርስዎ ጤና ይቀድማል።

3 ብቻዎን አይደሉም! ድጋፍ እና እርዳታ ያግኙ! ከድርጅ ቶች ወይም ከጓደኞችም ሆነ ከሚያውቋቸው ሠዎች። በደረሱብዎት ነገሮች እርስዎ ብቻዎን አይደሉም! ጉዳት ከደረሠባቸው ሌሎች ሠዎች ምክር ይጠይቁ፣ ያሉትን ኔትወርኮች ይጠቀሙ።

4 አስፈላጊ የሆኑ የትስስር ገጾች ሁሉ ዘለፋን ብቻ ሳይሆን ለምሳሌ የሀሠት ሪፖርቶችንም የሚከለክሉ መመሪያ ዎች አላቸው። የዚህ ዓይነት አስተያየቶች ካገጠሙ ዎት፣ የሪፖርት ማድረግ ይችላሉ፣ ማድረግም አለብ ዎት።
እንደ www.hassmelden.de ላሉ ገጾችም ሪፖርት ማድረግ ይጠቅማል።

5 ጥላቻውን ይጥቀሡ! በይፋ ቢሆን ይመረጣል። እን ደዚያ ሲያደርጉ ጉዳዩ ተራ ነገር ሳይሆን ቃላዊ ዘለፋ መሆኑን ሌሎች በግልጽ ያውቃሉ።

6 የምላሽ ንግግር: ምንም እንኳ አንባቢዎች ዝም የሚሉ እና ርምጃ የማይወስዱ ቢሆንም - የሀሠት ዜናን በመርህ ደረጃ መቃወም ይገባል። አንድ አስተያየት ውይ ይቱን ሊያቋርጥ፣ አዲስ አተያይ ሊያመጣ እና ለጥላቻ ንግግር ትኩረት ሊሠጥ ይችላል።

7 ነገር ግን: "አሠራጮችን አይመግቡ!" ድረ ገጽ ላይ ሆን ብለው ጥላቻን የሚያሠራጩ፣ ሌሎችን መተንኮስ እና መጉዳት የሚፈልጉ ተጠቃሚዎች አሉ። ምላሽ እየሠ ጧቸው መሆኑን ልብ ካሉ፣ ይሄ ሊያበረታታቸው እና ሊያ ነቃቸው ይችላል። የዚህ ዓይነት አካውንቶችን ብሎክ ማድረግ ወይም ሚዩት ማድረግ ይችላሉ።

አሠራጮችን አይመግቡ!

8 በደነ መረብ ሕግ አልቦ ስፍራ አይኋለም። እዚህም ክሶች ሊቀርቡ ይችላሉ - ለስም ማጥፋት፣ ለጥላቻ ቅስቀሳ ወይም ለጥቃት ቅስቀሳ። በሁሉም የጀርመን ግዛቶች ውስጥ ፖሊስ ኦንላይን አነፍናፊዎች አሉት። አብዛኛዎቹ የመንግስት አቃቤ ሕግ ጽ/ቤቶች ሪፖር ቶችን በኢሜይል ይቀበላሉ። ነገር ግን ይበሉ: ጉዳዩ ቀርቦ የሚሠማ ከሆነ፣ ሪፖርት የተኋረገበት ሠውም ስለ እርስዎ የሆነ ነገር ያውቃል።

9 አሠራጮችን ለማጋለጥ ሁልጊዜም ትርጉም የሚሠጥ ስክሪንሻት ይውሠዱ፣ ግጭቶችን ግልጽ ያድርጉ ወይም አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ ማስረጃ ያቅርቡ።



የኛ ፕሮጀክት - በጥላቻ ንግግር ላይ ማብቃት!

ጀርመን ውስጥ በርካታ ተቋማት በዘረኛነት እና በፀረሴማዊ ነት ላይ ይሠራሉ - የስደተኞች የራሳቸው አደረጃጀቶች ወይም ሌሎች አካባቢያዊ ማኅበራት።
የዚህ አይነት አደረጃጀቶች አብዛኛውን ጊዜ በጥላቻ ንግግር እንደተጠቁ የሚሠማቸው ሲሆን ከማኅበራዊ ትስስር ገጾች አፍረው ይሸሻሉ። እንደዚያም ቢሆን ስጋታቸውን በኅብረተሠቡ ውሥጥ ይበልጥ በስፋት እንዲታወቅ ማድረጋቸው አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

> **በፀረሴማዊነት እና በዘረኛነት የጥላቻ ንግግር ላይ ትስስር በመፍጠር እና በጋራ በመትጋት ለብዘኃ አብሮነት እና ለጠንካራ ኅብረተሠብ መፈጠር ማኅበረ - ፖለቲካዊ አግባብነታቸው ላይ አጽንኦት እንሠጣለን።**

የጥላቻ ንግግርን ለመቆጣጠር ጀርመን ውሥጥ አካባቢያዊ ተቋማትን ማብቃት እንፈልጋለን። ለጥቃቶች የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን እናስተምራለን፣ የምላሽ ንግግር ስልቶችን እናጎለብታለን፣ አጋርነት ተኮር ትብብርን ማምጣት እንደሚቻል እናሳያለን።

ከፍላጎታቸው ጋር በማጣጣም ለድርጅቶች በስልጠና፣ በኤሌክትሮኒክ የማስተማሪያ ዘዴ እና በምክር አገልግሎቶች ለምሳሌ ስላሉ አዝማሚያዎች፣ አገልግሎቶች፣ የማኅበረሠብ አስተዳደር፣ የደኅንነት እና የሪፖርት አውታሮች እናሳውቃለን።

ተጠሪ

ናቫ ዛራቢያን

ኢሜይል nzarabian@bs-anne-frank.de
→ www.bs-anne-frank.de

Bildungsstätte Anne Frank –
Zentrum für politische Bildung
und Beratung Hessen
Anne Frank የትምህርት ማዕከል –
የፖለቲካ ትምህርት እና የማማከር ማዕከል Hessen
Hansaallee 150
60320 Frankfurt am Main

bildungsstaette.anne.frank
BS_AnneFrank
bsannefrank

Bundesamt
für Migration
und Flüchtlinge